የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ-የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 18
ADDIS ABABA – February 17th 2006

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፺፰
የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፫ሺ፫፻፹፱

## CONTENTS

Regulation No. 122/2006
Tendaho Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulations ............................ Page 3389

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፺፰
### የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ ደንብ "የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>መቋቋም፤</u>
፩. የተንዳሆ የስኳር ፋብሪካ (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>
በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

ያንዱ ዋጋ
Unite Price 2.30

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 122/2006
### TENDAHO SUGAR FACTORY ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS

These Regulations are issued by the council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of powers and duties of The Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1) (a) of The public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*
These Regulations may be cited as the "Tendaho Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulations No. 122/2006"

2. *Establishment*
1) There is hereby established The Tendaho Sugar Factory (hereinafter the "Enterprise") as a public Enterprise.
2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*
A body to be designated by the Government shall be the Supervising Authority of the Enterprise.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O. Box 80,001

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አይሳይታ (በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር) ይሆናል። እንደ አስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩. የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ተክሎች ማልማት፤

፪. ስኳር ፣ የስኳር ውጤቶችንና የስኳር ተረፈ ምርቶችን በፋብሪካ ማምረት፤

፫. ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብና መሸጥ፤

፬. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ።

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፪ ነጥብ ዜሮ ፰ ቢሊዮን (ሁለት ቢሊዮን ሰማኒያ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፱ ነጥብ ፮ ሚሊዮን (ዘጠኝ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Aisaita (Afar Regional state) and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Objectives*

The objectives for which the Enterprise is established are the following:

1) to grow sugar cane and other sugar yielding plants;
2) to process and produce sugar, sugar products and sugar by-products;
3) to supply and sell its products in domestic and export markets;
4) to engage in any other related activities necessary for the attainment of its objectives.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise is Birr 2.08 billion of which Birr 9.6 million is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise may not be held liable beyond its total asset.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration

9. *Effective Date*

These Regulations shall come into force as of the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 8th Day of April 2006

Meles Zenawi

Prime Minister of

The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE